# ፍልሰታ ፡ ለማርያም ።

**'ሞትሰ ፡ ለመዋቲ ፡ ይደሉ ፤ ሞታ ፡ ለማርያም ፡ የበዕብ ፡ ለኵሉ ።'**

(ሞትስ፡ ለሟች፡ ይገባል፤ የማርያም፡ ሞት፡ ግን፡ ኹሉን፡ ያስደንቃል ።)

የሕይወት፡ እናት፡ እንዴት፡ ሞተች? መልአከ፡ ሞት፡ የአምላክን፡ እናት፡ እንዴት፡ እንደቀረባት፡ እጅግ፡ ያስደንቃል ። ቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ሰው፡ አንድ፡ መኾኗ፡ መጠን፡ በሰበሰችው፡ ሥጋ፡ *'አዳም፡ ዐፈር፡ ነኽ፤ ወደ፡ ዐፈር፡ ትመለሳለኽ'*፡ ባለው፡ ቃል፡ መሠረት፡ በዚህ፡ ዓለም፡ በሥጋ፡ ሞትን፡ ተጋርታለች ። ንጽሕትና፡ ቅድስት፡ እንደ፡ መኾኗ፡ መጠን፡ በሥጋ፡ ፈርሶና፡ በስብሶ፡ መቅረት፡ አላገኛትም ። ይኸንንም፡ እንደሚከተለው፡ እናያለን ።

**ፍልሰት**፡ ማለት፡ መለየት፡ ማረግ፡ ከምድር፡ ከመቃብር፡ ወደ፡ ላይ፡ መውጣት፡ ማለት፡ ነው ። ፍልሰታ፡ የሚለው፡ ቃል፡ የእመቤታችን፡ ሥጋ፡ ከጌቴ፡ ሴማኒ፡ ወደ፡ ገነት፡ ማረጉንና፡ በገነት፡ ዕፀ፡ ሕይወት፡ ሥር፡ ፪፻፭፡ ቀን፡ ከቈየ፡ በኋላ፡ መነሣቷን፡ የሚያስረዳ፡ ቃል፡ ነው ።

ቅዱስ፡ ያሬድ፡ በመዝሙሩ፡ *'ተለዐለት፡ እምድር፡ ወበሀየ፡ ነበረት፡ ዘምስለ፡ ወልዳ፡ በየማነ፡ አብ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ ።'* (እመቤታችን፡ ቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ከምድር፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ዐረገች፤ በሰማዩ፡ ከልጇ፡ ጋራ፡ በአብና፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ቀኝ፡ ተቀመጠች)፡ በማለት፡ እንደተናገረው ።

ጥንቱን፡ ሰው፡ የተፈጠረው፡ ለሞት፡ አልነበረም ። እናታችን፡ ሔዋን፡ ግን፡ ሕግን፡ በመተላለፍ፡ ምክንያተ፡ ስሕተት፡ ኾና፡ ያበላችን፡ የዕፀ፡ በለስ፡ ፍሬ፡ የሞት፡ ሞት፡ የሚያመጣ፡ ከገነት፡ የሚያስወጣ፡ ፍዳና፡ መርገም፡ በመኾኑ፡ ትውልድ፡ ኹሉ፡ በሞት፡ ጥላ፡ ተይዞ፡ ይኖር፡ ነበር ። አዳም፡ ለሚስቱ፡ **ሔዋ** [9]፡ ብሎ፡ ስም፡ አወጣላት፤ *ዘፍ. ፫፡ ፳* የሕያዋን፡ ኹሉ፡ እናት፡ ነሽ፡ ሲላት ። ነገር፡ ግን፡ የሕያዋን፡ ኹሉ፡ እናት፡ አልነበረችም፤ ርሷም፡ ልጆቿም፡ የሞት፡ ሞት፡ ተገዢ፡ ኹነው፡ ይኖሩ፡ ነበርና ። ከአዳም፡ እስከ፡ ሙሴ፡ ድረስ፡ ሞት፡ ነግሡ፡ እንደተባለ ። *ሮሜ. ፭፡ ፲፬*

ተፈጥሮው፡ ከሥጋና፡ ከሕያውት፡ ነፍስ፡ የኾነው፡ ሰው፡ ኹሉ፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ ዘመኑ፡ በተፈጸመ፡ ጊዜ፡ ሥጋና፡ ነፍሱ፡ በሞት፡ ተለያይተው፡ ሥጋ፡ ወደተገኘበት፡ መሬት፡ ነፍስም፡ ወደ፡ ሲኦል፡ ትኼድ፡ ነበር ። የሰውነት፡ መሞት፡ የነፍስ፡ ከሥጋ፡ መለየት፡ ሲኾን፤ **የነፍስ ፡ መሞት**፡ ደግሞ፡ የነፍስ፡ ከእግዚአብሔር፡ መለየት፡ ነውና ። ይህን፡ የሥጋና፡ የነፍስ፡ ሞት፡ ማንም፡ በዕውቀቱ፡ በኃይሉና፡ በሀብቱ፡ ሊያመልጠው፡ የማይቻል፡ ስለኾነ፡ ሴቱንም፡ ወንዱንም፡ ትልቁንም፡ ትንሹንም፡ ከአቤል፡ ጀምሮ፡ ኀጥኡንም፡ ጻድቁንም፡ ኹሉንም፡ ያግዝ፡ ነበር ።

በእግዚአብሔር፡ ቸርነትና፡ ርኅራኄ፡ የአበው፡ ጸሎትና፡ ተስፋ፡ የነቢያት፡ ትንቢትና፡ ምሳሌ፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፡ ዘመኑ፡ በደረሰ፡ ጊዜ፡ የተስፋው፡ ምልክት፡ የኾነችው፡ አማናዊቷ፡ ሔዋን፡ የሕያዋን፡ ኹሉ፡ እናት፡ ቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ በዚህ፡ ዓለም፡ ለአዳምና፡ ሔዋን፡ ዘር፡ ኹሉ፡ ምክንያተ፡ ድኅነት፡ ኾና፡ ከሃናና፡ ኢያቄም፡ ተወለደች ። *ኢሳ. ፩፡ ፱*

ቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ከእናቷ፡ ማሕፀን፡ ጀምሮ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ በማይነገርና፡ በማይመረመር፡ ንጽሕናና፡ ክብር፡ በውነት፡ ቀደሳት፡ አከበራት ። አዳም፡ *'ክፉ፡ አገደ፡ አገዱ፡ ኾነ'*፡ ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ በተናገረ፡ ጊዜ፡ ከአዳም፡ ዘር፡ ሥጋ፡ ኹሉ፡ የማርያምን፡ ሥጋ፡ በዘር፡ አደረገው ። የማርያም፡ ሥጋ፡ ከአዳም፡ ልጆች፡ ምስጋና፡ በፊት፡ በሰራዊት፡ ጌታ፡ በእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ተመሰገነ፤ ከበረ ። የሔዋን፡ ልጅ፡ ማርያም፡ በናት፡ አባቷ፡ ቤት፡ ሦስት፡ ዓመት፡ ቈይታ፡ ወደ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ አስገቧት ። በቤተ፡ መቅደስ፡ ዐሥራ፡ ኹለት፡ ዓመት፡ ቈይታ፡ ባሥራ፡ ዐምስት፡ ዓመቷ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ግብር፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ያለሩካቤ፡ ፀንሰች፤ ያለ፡ ጭንቅና፡ ያለ፡ ምጥ፡ ያለ፡ ልብ፡ ሐዘንም፡ በድንግልና፡ ፈጣሪዋን፡ ወለደችው ። እንዲሁም፡ በሔዋን፡ የገነት፡ በር፡ ተዘጋ፤ ዳግመኛም፡ በቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ተከፈተልን ። ከዕፀ፡ ሕይወት፡ እንበላ፡ ዘንድ አደለን፤ ይኸውም፡ ቅዱስ፡ ሥጋውና፡ ክቡር፡ ደሙ፡ ነው፡ በማለት፡ ቅዱስ፡ ኤፍሬም፡ እንደመሰከረው ።

ቅድመ፡ ዓለም፡ አባቱ፡ ያልቀደመው፤ እናቱን፡ የቀደመ፡ ልጅ፤ ልጇ፡ የቀደማት፡ እናት፤ እናቱን፡ የፈጠረ፡ ልጅ፤ ፈጣሪዋን፡ የወለደች፡ እናት፤ አባቷ፡ ሲኾን፡ ልጇ፡ ልጇም፡ ሲኾን፡ አባቷ፡ የኾነላት፡ ድንግል፤ አምላኳን፡ የወለደች፡ እናት፡ ልጇ፡ በከበረ፡ ደሙ፡ ያዳናቸው፡ የምእመናን፡ እናት፡ ነችና፡ የሞቷና፡ የትንሣኤዋ፡ ነገር፡ ዕፁብ፡ ድንቅ፡ ነው ። ልዩ፡ ከኾነች፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ይህ፡ ያምላክ፡ መወለድ፡ ምን፡ ይደንቅ፡ ምን፡ ይረቅ? ቃልን፡ ወሰነችው፤ ልደቱንም፡ ዘር፡ አልቀደመውም ። በመወለዱም፡ ድንግልናዋን፡ አልለወጠውም ። ቃል፡ ከአብ፡ ያለድካም፡ ወጣ፤ ከድንግልም፡ ያለሕማም፡ ተወለደ፤ እንዳለ፡ ቅዱስ፡ ኤፍሬም ።

ስለዚህ፡ የማርያም፡ ሥጋ፡ ክብር፡ እንደ፡ ነቢያትና፡ እንደ፡ ሐዋርያት፡ እንደ፡ ጻድቃንና፡ እንደ፡ ሰማዕታት፡ ሥጋ፡ ክብር፡ አይደለም ። ከሦስቱ፡ አካላት፡ አንዱ፡ አካል፡ ወልድ፡ የተዋሐደው፡ ቅዱስና፡ ክቡር፡ አካል፡ ነው፡ እንጂ፡ [illegible] ክርስቶስ፡ ከተዋሐደው፡ የማርያም፡ ሥጋ፡ በቀር፡ ለአዳም፡ እንድስ፡ እንኳ፡ መድኃኒት፡ አልኾነውም ።

ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የሰውን፡ ልጅ፡ ኹሉ፡ ከኃጢአት፡ ከመርገም፡ ከሞት፡ ሞት፡ ለማዳን፡ ሲል፡ ከድንግል፡ ማርያም፡ በተዋሐደው፡ ሥጋ፡ የኛን፡ ሞት፡ ለርሱ፡ ወስዶ፡ የርሱን፡ ሕይወት፡ ለኛ፡ በመስጠት፡ ሦስት፡ ቀንና፡ ሦስት፡ ሌሊት፡ በከርሠ፡ መቃብር፡ ዐድሮ፡ በራሱ፡ ሥልጣን፡ ባባቱ፡ አብ፡ በባሕርይ፡ ሕይወቱ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ሥልጣን፡ ሞትን፡ ድል፡ አድርጎ፡ ልዩ፡ በኾነ፡ ትንሣኤው፡ **የሙታን ፡ በኵር ፡ ኾኖ ፡ ተነሣ** ። *ቆላ. ፩፡ ፩-፲፰፤ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፭፡ ፳፫*

ቅዱስ፡ አትናቴዎስ፡ ይህን፡ አንቀጽ፡ ሲተረጕም፡ *'በኵር፡ የተባለው፡ ከኛ፡ አስቀድሞ፡ ስለሞተ፡ አይደለም ። ነገር፡ ግን፡ ስለኛ፡ ሙቶ፡ ሞትን፡ ድል፡ በመንሣቱ፡ ትንሣኤን፡ በርሱ፡ ክርሱ፡ በኋላ፡ ስለምናገኘው፡ ነው'*፡ ብሏል ። በመቀጠልም፡ *'በልዩ፡ ትንሣኤውም፡ ሰውን፡ ዳግመኛ፡ ወደ፡ ገነት፡ መለሰው'*፡ በማለት፡ ቅዱስ፡ ኤፍሬም፡ እንዳስተማረው ።

አባቷ፡ ዳዊትም፡ *'አቤቱ፡ ወደ፡ ዕረፍትኽ፡ ተነሥ፡ አንተና፡ የመቅደስኽ፡ ታቦት'*፡ *መዝ. ፻፴፩፡ ፰* እንዳለው ። አንድም፡ አንተ፡ ፈጣሪዬ፡ ሆይ፡ ሦስት፡ መዓልትና፡ ሦስት፡ ሌሊት፡ በከርሠ፡ መቃብር፡ አድረኽ፡ መግነዝ፡ ፍቱልኝ፡ መቃብር፡ ክፈቱልኝ፡ ሳትል፡ ከንቱም፡ መቃብር፡ በራስኽ፡ ሥልጣን፡ ከሙታን፡ ተለይተኽ፡ ለምእመናን፡ ዕረፍት፡ ወደምትሰጥበት፡ ወደ፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ተነሣ ። አንተ፡ ብቻ፡ ሳትኾን፡ የመቅደስኽ፡ ታቦት፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋ፡ ከነፍሷ፡ ነፍስ፡ ተዋሕደኽ፡ ሰው፡ ኾንኽ፡ ፱፡ ወር፡ ካ፭፡ ቀን፡ አንተ፡ እንደ፡ ጽላት፡ ኾንኽ፡ ማሕፀኗን፡ ታቦት፡ አድርገኽ፡ ያደረክባት፡ እናትኽ፡ ቅድስት፡ ማርያም፡ መግነዝ፡ ፍቱልኝ፡ መቃብር፡ ክፈቱልኝ፡ ሳትል፡ ከንቱም፡ መቃብር፡ ባንተ፡ ሥልጣን፡ ትነሣ ።

ዳግመኛም፡ *'በወርቅ፡ ልብስ፡ ተጐናጽፋ፡ ተሸፋፍና፡ ንግሥቲቱ፡ በቀኝኽ፡ ትቆማለች ።'* *መዝ. ፵፬፡ ፰* አንድም፡ ንግሥተ፡ አርያም፡ ቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ በውስጥ፡ በአፍአ፡ በነፍስ፡ በሥጋ፡ ፍጽምት፡ ኾና፡ ንጽሐ፡ ነፍስ፡ ንጽሐ፡ ሥጋ፡ ንጽሐ፡ ልቦና፡ አንድ፡ አድርጋ፡ ይዛ፡ በክብር፡ በቅድስና፡ በቀኝኽ፡ ትቆማለች፡ በማለት፡ ሲናገር፡ ጠቢቡ፡ ሰሎሞንም፡

*'ወዳጄ፡ ሆይ፡ ተነሽ፤*
*ውብቴ፡ ሆይ፡ ነይ፤*
*እንሆ፡ ክረምቱ፡ ዐለፈ፡*
*ዝናቡም፡ ዐልፎ፡ ኼደ፤*
*አበቦች፡ በምድር፡ ላይ፡ ተገለጡ፡*
*የዜማም፡ ጊዜ፡ ደረሰ፤*
*የቍርቁዎ ችም፡ ቃል፡ በምድራችን፡ ተሰማ ።*
*በለሱ፡ ጐመራ፡ ወይኖችም፡ አበቡ፤*
*መዓዛቸውንም፡ ሰጡ ።*
*ወዳጄ፡ ሆይ፡ ተነሽ፤*
*ውብቴ፡ ሆይ፡ ነይ ።'* *መሐ. ፪፡ ፲*

በማለት፡ ከዘመናት፡ በፊት፡ ተናግሯል ። ወዳጁን፡ እናቱን፡ ውብቱን፡ ቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያምን፡ *'ተነሺ፤ ነይ'*፡ እያለ፡ በነቢያቱ፡ እንደበት፡ የተጣራው፡ ጌታችን፡ መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ነው ። ካህኑ፡ ሰሎሞንም፡

---

9 **'ወሰመየ ፡ አዳም ፡ ስመ ፡ ብእሲቱ ፡ ሔዋ ፤ እስመ ፡ ይእቲ ፡ እመ ፡ ኵሉ ፡ ሕያዋን ።'** *ዘፍ. ፫፡ ፳ ።*

www.ethiopianorthodox.org

*'ባንቺም ፡ ደግሞ ፡ በነፍስሽ ፡ ሰይፍ ፡ ያልፋል '፡ ሉቃ. ፪ ፥ ፴፭* በማለት ፡ እንደተናገረው ።

ልቧ ፡ በሐዘን ፡ ፍላጻ ፡ ሲነደፍ ፡ የኖረች ፡ የመከራ ፡ ክረምት ፡ ካለፈ ፥ የክርስቶስ ፡ ሕማሙ ፡ ስቅለቱ ፡ ሞቱ ፡ ቤዛነቱ ፡ ከተፈጸመ ፥ ትንሣኤው ፡ ዕርገቱ ፡ ዳግም ፡ ምፅአቱ ፡ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከተሰበከ ፥ የሐዋርያት ፡ ድምፅ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ከተሰማ ፥ የወንጌል ፡ አዝመራ ፡ መታየት ፡ ከጀመረ ፥ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በሃይማኖት ፡ ማበብና ፡ ማፍራት ፥ መዓዛ ፡ ምግባራቸውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማቅረብ ፡ ከጀመሩ ፡ በኋላ ፥ እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያምን ፡ ጌታችን ፡ በዕፀ ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ ኾኖ ፡ የሚወደውን ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስን ፤ *'እንኋት እናትኽ ' ዮሐ. ፲፱ ፥ ፳፯* ካለው ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ላ፲፭ ፡ ዓመታት ፡ እዮሐንስ ፡ ቤት ፡ ኖራ ፥ ባ፵፱ ፡ ዓ. ፡ ም. ፥ ፷፬ ፡ ዓመት ፡ ሲኾናት ፥ ጥር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ ዕረፍት ፡ መለየቷን ፡ ያስተምራል ።

ካረፈችበት ፡ ከጥር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፥ ከቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ ተለይታ ፡ በገነት ፡ በዕፀ ፡ ሕይወት ፡ ሥር ፡ ለኹለት ፡ መቶ ፡ አምስት ፡ ቀናት ፡ ቈይታ ፡ ሥጋዋን ፡ መፍረስ ፡ መበስበስ ፡ ሳያገኘው ፥ ትንሣኤ ፡ ዘጉባኤን ፡ ሳትጠብቅ ፡ ነሐሴ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ መቃብር ፡ ከፈቱልኝ ፡ መግነዝ ፡ ፍቱልኝ ፡ ሳትል ፥ ድጋሜ ፡ ሞት ፡ በሌለበት ፡ ትንሣኤ ፡ ልጇን ፡ አብነት ፡ አድርጋ ፡ በርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ከሞት ፡ ተነሥታለች ።

ስለዚህ ፥ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የሰማችውን ፡ ምስጋና ፡ የሰማ ፥ የወለደችውን ፡ ቅዱስ ፡ የወለደ ፥ የተሸከመችውን ፡ መለኮት ፡ የተሸከመ ፥ የኾነችውን ፡ ቅድስና ፡ የኾነ ፥ ያገኘችውን ፡ ጸጋ ፡ ያገኘ ፥ የከበረችውን ፡ ክብር ፥ ከፍጡራን ፡ ወገን ፡ የለምና ። የአብ ፡ ቃል ፥ እናቱ ፥ ቅድስት ፥ ድንግል ፡ ሆይ ፤ ስላንቺ ፡ የሚነገረውን ፡ ነገር ፡ መናገር ፡ የሚቻለው ፡ ምን ፡ እንደበት ፡ ነው ። እንዳለው ፡ ቅዱስ ፡ ኤፍሬም ። *ታሪክ ፡ ዘኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን*

የእመቤታችን ፡ የቅድስት ፡ ድንግል ማርያም ፡ ዕረፍት ፡ በኾነበት ፡ ዕለት ፥ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ አስከሬንዋን ፡ ለማሳረፍ ፡ ወደ ፡ ጌቴ ፡ ሰማኒ ፡ መካነ ፡ ዕረፍት ፡ (የመቃብር ቦታ) ፡ ይዘው ፡ ሲኼዱ ፥ አይሁድ ፡ በቅናት ፡ መንፈስ ፡ ተነሣሥተው ፥ *'ቀድሞ ፡ ልጇ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ ተነሣ ፤ ባርባኛው ፡ ቀኑ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ፤ እንደገናም ፡ ተመልሶ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ለማሳለፍ ፡ ይመጣል ፡ እያሉ ፡ በማስተማር ፡ ሕዝቡን ፡ ፈጽመው ፡ ወሰደውታል ። አኹን ፡ ደግሞ ፡ ዝም ፡ ብለን ፡ ብንተዋት ፥ ርሷንም ፡ እንደ ፡ ልጇ ፡ ተነሣች ፥ ዐረገች ፡ እያሉ ፡ በማስተማር ፡ ሊያውኩን ፡ ሊኖሩ ፡ አይደለምን? ኑ! ተሰበሰቡና ፡ በእሳት ፡ እናቃጥላት '*፡ ብለው ፡ ተማክረው ፡ መጥተው ፥ ከመካከላቸው ፡ ታውፋንያ ፡ የተባለ ፡ ጕበዝ ፡ አይሁዳዊ ፡ ተመርጦ ፡ ኼዶ ፥ የእመቤታችንን ፡ አስከሬን ፥ የተሸከሙበትን ፡ አልጋ ፡ ሸንኮር ፡ ያዘ ። የአልጋውን ፡ ሸንኮር ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ በእሳት ፡ ሰይፍ ፡ ኹለት ፡ እጆቹን ፡ ስለቈረጣቸው ፥ ካልጋው ፡ ሸንኮር ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥለው ፡ ቀሩ ። ነገር ፡ ግን ፥ ታውፋንያ ፥ በፈጸመው ፡ ድርጊት ፡ ተጸጽቶ ፡ ወደ ፡ እመቤታችን ፡ ስለተማጸነ ፥ በንቡዕ ፡ ተአምር ፥ የተቈረጡ ፡ እጆቹን ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ አድርጋ ፡ ፈውሳዋለች ።

በዚያ ፡ ጊዜም ፡ መልአክ ፡ እግዚአብሔር ፥ የእመቤታችንን ፡ አስከሬን ፡ ከሐዋርያው ፡ ዮሐንስ ፡ ጋራ ፥ ነጥቆ ፡ ወስዶ ፥ በገነት ፥ በዕፀ ፡ ሕይወት ፡ ሥር ፡ አስቀመጠው ። ቅዱስ ፡ ዮሐንስም ፥ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፥ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ሲመጣ ፥ የእመቤታችን ፡ አስከሬን ፡ በገነት ፡ መኖሩን ፥ ነገራቸው ። ሐዋርያትም ፡ የእመቤታችንን ፥ አስከሬን ፡ ለማግኘት ፥ ከነበራቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ ምኞትና ፡ ጕጕት ፡ የተነሣ ፥ በነሐሴ ፡ ፩ ቀን ፡ ሱባኤ ፡ ገብተው ፡ ሲጸሙና ፡ ሲጸልዩ ፡ ከሰነበቱ ፡ በኋላ ፥ ባሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ (በኹለተኛው ፡ ሱባኤ ፡ መጨረሻ) ፥ ጌታችን ፡ የእመቤታችንን ፡ ቅዱስ ፡ አስከሬን ፡ አምጥቶ ፥ ስለሰጣቸው ፥ በታላቅ ፡ ዝማሬ ፥ በውዳሴና ፡ በጽኑ ፡ መሕላ ፡ ወስደው ፥ ቀድሞ ፡ በተዘጋጀው ፡ መካነ ፡ ዕረፍት ፡ በጌቴ ፡ ሴማኒ ፡ ቀበሯት ።

የእመቤታችን ፡ የቀብር ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ ካሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ አንዱ ፡ የኾነው ፡ ቅዱስ ፡ ቶማስ ፡ አልነበረምና ፥ ከሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ በዳመና ፡ ተጭኖ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሲመጣ ፥ እመቤታችን ፡ በተቀበረች ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፥ እንደ ፡ ልጇ ፡ ትንሣኤ ፡ ተነሥታ ፡ ስታርግ ፡ ያገኛታል ። በዚያ ፡ ጊዜ ፥ ትንሣኤዋን ፡ ሌሎቹ ፡ ሐዋርያት ፡ አይተው ፥ ለርሱ ፡ የቀረበት ፡ መስሎት ፡ ተበሳጭቶ ፥ *'ፈቀደ ፡ ይደቅ ፡ እምደመናሁ '* ይለዋል ፤ ማለት ፥ በፊት ፡ የልጅሽን ፡ ትንሣኤ ፡ አኹን ፡ ደግሞ ፡ ያንቺን ፡ ትንሣኤ ፡ ሳላይ ፡ ቀረሁ ፡ ብሎ ፡ ከማዘኑ ፡ የተነሣ ፥ ከደመናው ፡ ተወርውሮ ፡ ሊወድቅ ፡ ቃጣው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፥ እመቤታችን ፥ ከርሱ ፡ በቀር ፡ ሌሎቹ ፡ ሐዋርያት ፡ ትንሣኤዋን ፡ እንዳላዩ ፡ ነግራው ፥ ቅዱስ ፡ ቶማስን ፡ አጽናናችው ። ኼዶም ፥ ለወንድሞቹ ፡ ለሐዋርያት ፡ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ እንዲነግራቸው ፡ አዛው ፥ ለምልክት ፡ ምስክር ፡ ይኾነው ፡ ዘንድ ፥ የተገነዘበችበትን ፡ ሰበኗን[10] ፡ ሰጥታው ፥ ፈጽማ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐርጋለች ።

ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ቶማስም ፥ ሐዋርያት ፡ ወዳሉበት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥ *'እመቤታችንን ፡ እኮ ፡ ቀበርናት '*፡ ብለው ፡ ነገሩት ። ርሱም ፥ ዐውቆ ፡ ምስጢሩን ፡ ደብቆ ፥ *'አይደረግ! ሞት ፡ በጥር ፥ በነሐሴ ፡ መቃብር ፡ እንደምን ፡ ይኾናል?'*፡ አላቸው ፤ *'አንተ ፡ እንጂ ፡ ቀድሞ ፡ የጌታን ፡ ትንሣኤ ፡ ተጠራጠርክ ፥ አኹንም ፡ አታምንምን?'* ብለው ፥ በቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ መሪነት ፥ ወደመቤታችን ፡ መካነ ፡ መቃብር ፡ ይዘውት ፡ ኼደው ፡ ሊያሳዩት ፡ መቃብር ፡ ቢከፍቱ ፥ የእመቤታችንን ፡ አስከሬን ፡ ዐጡት ፤ ደነገጡ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፥ ቅዱስ ፡ ቶማስ ፥ *'አታምኑኝም ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ እመቤታችን ፡ ተነሥታ ፡ ዐርጋለች '*፡ ብሎ ፥ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ ከተረከላቸው ፡ በኋላ ፥ ለማረጋገጫ ፡ ምልክት ፡ እንዲኾን ፡ የሰጠችውን ፡ ሰበኗን ፡ አሳያቸው ። እነርሱም ፥ ሰበኗን ፡ ለበረከት ፡ ቈራርጠው ፡ ከተከፋፈሉ ፡ በኋላ ፥ ወደየአህጉረ ፡ ስብከታቸው ፡ ኼደዋል ።

ባመቱ ፥ ትንሣኤሽን ፡ ቶማስ ፡ አይቶ ፡ እኛ ፡ እንዴት ፡ ይቅርብን ፡ ብለው ፥ ከነሐሴ ፡ ፩ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሱባኤ ፡ ገቡ ። በሱባኤው ፡ መጨረሻም ፥ በነሐሴ ፡ በ፲፮ው ፡ ቀን ፥ ጌታችን ፡ የለመኑትን ፡ ልመና ፡ ተቀብሎ ፥ እመቤታችንን ፡ መንበር ፥ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስን ፡ ንፍቅ ፡ (ረዳት) ፡ ቄስ ፡ ቅዱስ ፡ እስጢፋኖስን ፡ ገባሬ ፡ ሠናይ ፡ (ዋና) ፡ ዲያቆን ፡ አድርጎ ፥ ቀድሶ ፥ ኹሉንም ፡ ካቈረባቸው ፡ በኋላ ፥ የእመቤታችን ፡ ዕርገቷን ፡ ለማየት ፡ አብቅቷቸዋል ።

ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፥ ሐዋርያዊቷ ፥ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፥ ሥርዐት ፡ ሠርታ ፥ ከሰባቱ ፡ አጽዋማት ፡ ተርታ ፡ አስገብታ ፥ ይህን ፡ ታላቅ ፡ የበረከትና ፡ የሚስጢር ፡ መግለጫ ፡ ጾም ፡ ትጾማለች ። በጽኑ ፡ ለሚፈልጉት ፡ ኹሉ ፡ የሚሰጠውን ፥ ለሚገባቸውም ፡ ተትረፍርፎ ፡ የሚናኘውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋና ፡ በረከት ፡ ለማግኘት ፥ ሐዋርያት ፡ ያዩትን ፡ ድንቅ ፡ ምስጢር ፡ የእመቤታችንን ፡ ትንሣኤና ፡ ዕርገት ፡ ለማየትና ፡ ከሐዋርያት ፡ አበው ፡ በረከት ፡ ለማሳተፍ ፡ ጌታችን ፡ 'ደቂቅየ ፤ ልጆቼ ' ፡ ይላቸው ፡ በነበሩት ፡ ሐዋርያት ፡ አምሳል ፥ ሕፃናትና ፡ ወጣቶች ፥ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፥ አረጋውያንም ፥ የጾመ ፡ ፍልሰታን ፡ መድረስ ፡ በናፍቆት ፡ እየጠበቁ ፥ በያመቱ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ያከብሩታል ። በዚህ ፡ የእመቤታችን ፡ ትንሣኤና ፡ ዕርገት ፡ መታሰቢያ ፡ (በጾመ ፍልሰታ) ፡ ወቅት ፥ ብዙዎች ፡ ከቤታቸው ፡ ተለይተው ፥ በመቃብር ፡ ቤት ፡ ዘግተው ፥ አልጋና ፡ ምንጣፍ ፡ ትተው ፥ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፥ ዝግኝ ፡ ጥሬ ፥ እፍኝ ፡ ውሃ ፡ እየቀመሱ ፥ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ በመትጋት ፥ በታላቅ ፡ ተጋድሎ ፡ ይሰንብታሉ ። ይህም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምእመናን ፡ ለእመቤታችን ፡ ያላቸውን ፡ ጽኑና ፡ ጥልቅ ፡ ፍቅር ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ነው ።[11]

የሔዋንና ፡ የአዳም ፡ ካሳ ፡ የተከፈለባት ፤

ጥንተ ፡ ኀጢአት ፡ ፍርሀተ ፡ ሞት ፡ ድል ፥ የተነሣባት ፤

መርገመ ፡ ሔዋን ፡ መርገመ ፡ አዳም ፡ የተሰረየባት ፤

የዲያብሎስ ፡ ምርኰኛነት ፡ የኀጢአት ፡ ባርነት ፡ የተወገደባት ፤

የነፍስ ፡ መድኀኒት ፥ የሕይወት ፡ ምግብ ፡ የተገኘባት ፤

ቅድመ ፡ ፀኒስ ፥ ጊዜ ፡ ፀኒስ ፥ ድኅረ ፡ ፀኒስ ፡ ድንግል ፤

ቅድመ ፡ ወሊድ ፥ ጊዜ ፡ ወሊድ ፥ ድኅረ ፡ ወሊድ ፡ ድንግል ፤

እንበለ ፡ ዘርዕ ፥ እንበለ ፡ ሩካቤ ፥ እንበለ ፡ ሰስሎተ ፡ ድንግልና ፡ ፀንሳ ፡ የወለደች ፤

ድንግል ፡ በሥጋ ፡ ወበኅሊና ፤

እናትነትን ፡ ከድንግልና ፥ ድንግልናን ፡ ከናትነት ፡ አስተባብራ ፡ የተገኘች ፡ ድንግል ፡ ወእም ፡ እመቤታችን ፥ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ናት ።

የክርስትናን ፡ እምነት ፡ በናትነት ፡ ለመቀበል ፡

---

10 ሰበን ፤ ያንገትን ፡ የራስ ፡ የትከሻ ፡ ልብስ ፡ ሻል ፡ ሞጣሕት ፤ በላይ ፡ የሚለበስ ። (አዘጋጅ)

www.ethiopianorthodox.org

11 *ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፤ ገጽ ፡ 110ን ፡ ይመልከቱ ።*

የመጀመሪያዋ እንደሆነች ሁሉ እንዲሁም ለሰው ልጆች ሁሉ ተስፋ ሆና በእምነት የሚጠበቀውን የዘለ ዓለም ሕይወት ትንሣኤን በቅድምና ታድላለች።

ስለዚህ ምእመናን ሆይ፤ የእመቤታችን ክብሯ፣ ቅድስናዋ፣ አማላጅነቷ፣ ምስጋናዋ መቼም ቢሆን እንደ ማያቋርጥና እንደ ቅዱስ ገብርኤልና እንደ ቅድስት ኤልሳቤጥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የፈቀደላቸውና የገለጠላቸው ምእመናን ሁሉ፤ ቅድስት፣ ውድስት ቡርክት ነሽ እያሉ ሲያመሰግኗት ይኖራሉ፤ ከልጆሽ ከወዳጆሽ አማልጂን እያሉ ይማጸናሉ። ርሷም ከልጇ ከአማኑኤል አማልዳ በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን ታሰጣለች።

የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል አማላጅነት አይለየን፤ አሜን።

አባ ግርማ ከበደ

በዜና ደብረ ጽዮን ላይ ከጻፉት የተወሰ www.ethiopianorthodox.org

መስከረም-የካቲት 1996